የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ኤምባሲ ብራሰልስ
Embassy of The Federal Democratic
Republic of Ethiopia – Brussels

ቀን፣ Date 11/2/2013
ቁጥር፣ Ref. No. BE/Com/n/52/13

# የኢትዮጵያ ታላቁ ህዳሴ ግድብ

## I. ቦንድ ግዥ

የታላቁ ህዳሴ ግድብ የሚያስፈልገውን ከፍተኛ የፋይናንስ መጠን ከሀገሪቱ ተወላጆች በማሰባሰብ ዕውን ለማድረግ እንዲቻል የቀረበ የቦንድ ኩፖን ነው።

### 1. ቦንድ ለመግዛት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

- በሀገር ወስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያወያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን
- የአባይ ተፋሰስ የጎረቤት አገሮች ዜጎች መግዛት ይችላሉ
- የፓስፖርት ወይም የትውልደ ኢትዮጵያዊያን መታወቂያ ኮፒ ወይም ማንኛውም ኢትዮጵያዊነትን የሚገልጽ ሰነድ
- የፓስፖርት መጠን ያላቸው ሁለት ፎቶግራፍ
- የህዳሴ ቦንድን ለሁለተኛ ሰው ማስተላለፍ ይቻላል
- የህዳሴ ቦንድ ዕድሜአቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች በወላጆቻቸው አማካኝነት ቦንድ መግዛት ይቻላል

### 2. የቦንዱ ጠቀሜታዎች

- በቁጠባ ሀብት ለመፍጠር ማስቻሉ እና የቁጠባ ባህልን ለማዳበር መርዳቱ
- በታሪካዊው የህዳሴ ግድብ ግንባታ ተሳታፊ በመሆን የሚገኝ የመንፈስ እርካታ
- ለሀገር ልማት የሚያሰፈልገውን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ማሳደግ ማስቻሉ
- ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ተጨማሪ የስራ ዕድል መፍጠር ማስቻሉ ናቸው

### 3. የህዳሴ ቦንድ ዋና ባህሪያት

- ቦንዱ ወለድ የሚከፈልበት ሲሆን በገዥው ፍላጎት ከወለድ ነጻ መግዛት ይቻላል
- ቦንዱ ከተገዛበት ዕለት ጀምሮ ወለድ ይታሰባል
- ወለድ የሚታሰበው በየስድስት (6) ወራቱ ሲሆን ከገቢ ግብር ነጻ ነው
- ከወለድ የሚገኘውን ገንዘብ ሌላ ተጨማሪ ቦንድ ለመግዛት ወይም በውጭ ምንዛሬ /ብር የባንክ ሂሳብ ከፍቶ ገቢ ማድረግ ወይም ሌሎች ለልዩ ልዩ ክፍያዎች ማዋል ይቻላል
- ቦንዱን በማስያዝ ከሀገር ውስጥ ባንኮች ብድር መውሰድ ይቻላል
- ቦንዱ የመንግስት ሙሉ ዋሰትና ያለው በመሆኑ መቶ(100%) አስተማማኝ ነው

**የወለድ መጠን የሚታሰበው**

- 5 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላለው----------------LIBOR+1.25 በመቶ
- ከ6-7 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላላቸው------- LIBOR+1.5 በመቶ
- ከ8-10 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላላቸው------- LIBOR+ 2 በመቶ
- **LIBOR: London Interbank Offer Rate** ማለት በለንደን የገንዘብ ገበያ ባንኮች በየዕለቱ እርስ በእርሳቸው የሚበዳደሩበት የወለድ መጣኔ ነው።

Avenue de Tervuren. 64 • B- 1040 Brussels
Tel. : 00 32 2 771 32 94 • Fax : 00 32 2 771 49 14
Email : info@ethiopianembassy.be • www.ethiopianembassy.be

4. **የቦንዱ ዋጋ እና የክፍያ ጊዜ**
  - ዝቅተኛው የቦንድ ዋጋ 50 ዩሮ ሆኖ ባለ 100 ፣300 ፣500፣ 1,000 ፣3,000 ፣5,000 እና 10,000 የቦንድ ኩፖኖች ለሽያጭ ቀርበዋል
  - ዝቅተኛው የክፍያ ጊዜ 5 ዓመት ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 10 ዓመት ነው
5. **የህዳሴ ቦንድ የዋና ገንዘብ ክፍያ ሁኔታ**
  - የቦንዱ ጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ ዋናውን ተመላሽ ገንዘብ ከነወለዱ በውጭ ምንዛሬ መውሰድ፣ በሀገር ውስጥ በተከፈተ የውጭ ምንዛሬ /የብር ሂሳብ ገቢ ማድረግ ፣ሌላ ተጨማሪ ቦንድ ለመግዛት ወይም ከውጭ ለሚገቡ እቃዎች ክፍያ ለመጠቀም ይቻላል
  - የቦንዱ ሰርትፊኬት ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ አስፈላጊ ሰነዶችን አቅርቦ በምትኩ ማስረጃ መውሰድ ይቻላል
  - ቦንዱ በሙሉ ወይም በከፊል ቢበላሽ ለኤምባሲው በማሳወቅና የተበላሸውን በመመለስ ሌላ ማስረጃ ይሰራለታል

## II. ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ስጦታ ለመለገስ

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአገር ውስጥም በውጭም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ህዝቦች ከፍተኛ ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ :: በአሁኑ ሠዓት ከመቸውም በላይ የህዝብ ድጋፍ የሚጠይቅበት ደረጃ ላይ በመድረሱ እንደጀመርነው ለመጨረስ እና አሻራችንን ለማኖር ቁርጠኝነታችንን ማሳይት ይጠበቅብናል::

በመሆኑም የግድቡን ግንባታ በሚፈለገው ደረጃ ለማጠናቀቅ አቅም በፈቀደ ሁሉ ቦንድ ከመግዛት ባለፈ በገንዘብ ለመደገፍ እንዲቻል የስጦታ መቀበያ ህጋዊ ደረሰኝ የተዘጋጀ ስለአለ ማንኛውም ሰው በስጦታ መለገስ ይችላል:: ስጦታውን ለማድረግ ከዚህ በታች ያለውን ቅደም ተከተል ይጠቀሙ፣

6. **ተጨማሪ መረጃ**
  - ቦንድ ለመግዛት ወይም ስጦታ ለመለገስ በኢፌዲሪ ኤምባሲ ብራስልስ በአካል በመቅረብ ወይም በኢሜይል መረጃዎችን በመላክ በኦንላይን መግዛት ወይም መለገስ ይቻላል::

**የቦንድ ክፍያ ወይም ስጦታ ለመለገስ የባንክ ሂሳብ ቁጥር**

1. **Bank Name -ING**
2. **Account N0. BE 07 3631 2147 5766**
3. **Account beneficiary - FDRE EMBASSY BRUSSELS**
4. **BIC- BBRUBEBB**
5. **Communication - GERD bond purchase / donation/ በማለት ገንዘቡን ማስተላለፍ ይቻላል::**
6. **የባንክ ቅጹን ከሞሉና እና ገንዘቡን ካስተላለፉ በኋላ** በኤምባሲው ኢሜይል አድራሻ
7. **Email.** Diaspora.brussels@mfa.gov.et / ወይም
8. በስልክ ቁጥር 02 771 32 94 /0484 03 38 30 በማሳወቅ የቦንድ ኩፖኑ (የስጦታ ደረሰኝ ) በስምዎ ተዘጋጅቶ ይሠጠዎታል::

Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Consular Section Brussels

ብራስልስ የኢፌዲሪ ኤምባሲ

ዳያስፖራ ጉዳዮች